# የሰላም ትግል

ስለ ሰላማዊ የትግል ስልት ይህችን ጽሁፍ እንዳቀርብ ያነሳሳኝ ነገር በሚቀጥለው ድግሳችን ላይ ለሚደረገው የትግል ስልታችን ውይይት የሚቀርብ ወረቀት አመራሩ የትጥቅ ትግሉን ጎን አስመልክቶ የመንደርደሪያ ሐሳብ ሰላወረደ ምን አልባት የሰላማዊ ስልቱን በሚመለከት ደግሞ ይህችን ባቀርብ ለውይይት ማስጀመሪያ ልትሆን ትችላለች በሚል ሐሳብ ነው። ሊያጋጥሙን የሚችሉ ችግሮችን ሁሉ ለማሳየት ሞክሪያለሁ። አንዳንድ ሁኔታዎችን ከበድ አድርጌ ያቀረብኩት ዙሪያ ገደሉን ለማካበድ ብዬ ሳይሆን ኮስተር ብለን መምረጥ የሚገባንን የትግል ስልት አስተካክለን ወደፊት ለመጓዝ መቻል አለብን ብዬ ስላሰብኩ ነው። የሚጎድላትንና እኔ ለማየት ያልቻልኩትን ጓዶች እያሟሉ ለሙሉ ሕይዎት ያበቋታል ብዬ አምናለሁ።

የዴሞክራሲ ፋና በአምባ ገነን መንግስት ሀይል በተዳፈነበት አገር ውስጥ ሰላማዊ ትግል ማድረግ በጣም አስቸጋሪና ከፍተኛ መስዋትነት የሚጠይቅ መሆኑን የተለያዩ አገሮች ልምድ አስተምሮናል። በተለይም ሕዝብ ተደራጅቶና ተባብሮ ባልተ ዘጋጀበት አገር ውስጥ አንድ የፖልቲካ ድርጅት ዴሞክራሲያዊ ትግሉን ለማራመድ ከፍተኛ የሆነ መስዋዕትነት ሊከፍል ይችላል። ይሁን እንጂ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ደግሞ ይህን አስፈሪ መስዋዕትነት ከፍለው የዴሞክራሲን ጸዋ ተጎንጭተዋል። ለነጻነት የሚደርግ ትግል ከፍተኛ የሕይዎት ዋጋ እንደሚከፈልበት ማንም ታጋይ የሚገነዘበው ሐቅ ነው። ይህ መስዋዕትነትና እመቃ ተፈርቶ ተረግጦ ለመገዛት ጀርባን ማመቻቸት ሳይሆን የሚከፈለውን መስዋትነት ለመከፈል መዘጋጀትና መታገል የግድ ነው፤ ስለዚህ ተደራጅቶ አስፈላጊውን የትግል ስልት ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር አስማምቶ መታገል ከአፈናና ከጭቆና ነጻ ያወጣል፤ ሰፊውን ህዝብ ለስልጣን ያበቃል። ስለዚህ ነው ሐቀኛ ታጋይ ትግል ሚያስከፍለውን መስዋዕትነት ብቻ ሳይ ሆን ደህና ውጤቱን እያስቀደመ የምነቱ ስንደቅ በማድረግ ከትግል ጎራ የማይዛነፈው።

በማንኛውም ሚዛን ለነጻነት የሚደረግ ትግል ያለመስዋዕትነት አይመጣም። የመስዋዕትነቱ ሚዛን እንደ ተጨባጭ ሁኔታው ሊለያይ ይችላል። የሰላማዊ ትግል በትጥቅ ከሚደረግ ትግል የሚለየው በሚከፈለው መስዋዕትነት ማነስና መብዛት ይሆናል እንጂ በሁለቱም በኩል ከፍተኛ የሆነ የህይዎት ፤ የገንዘብ ፤ የጉልበት መስዋትነትን ያስከፍላል። በትጥቅ ትግል በኩል የሚደረግ ግጥሚያ በሁለቱም በኩል መሳሪያ የታጠቁ ሐይሎች ስለሚፋለሙ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ፤ የሶሻል፤ የኢኮኖሚና የባህል ቀውስ ያስከትላል። በህዝብም ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ቁስል ይተዋል፤ በትጥቅ ትግል አቸንፎ የገባ ኃይል ደግሞ ሁልጊዜ በጥርጣሬ አይን እንዲታይ ያደርገዋል። ይህኛውን መንገድ ከማንኛውም የአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች በበለጠ እኛ በተግባር

በተለይ ደግሞ እንደ ወያኔ ያለ አምባ ገነን መንግስት ከእኔ በቀር ማን አለ በሚልባት አገር ሁኔታውን የባሰ ያደርገዋል።

የሰላም ትግል ስንል እንዴት የሚለው ጥያቄ ሁልጊዜ ስለሚነሳ ጠቅለል ባለ መንገድ መመልከቱ ይበጃል፤

1. መንግስት በሚያወጣው ህግና ሜዳ ሰጥ ለጥ ብሎ በጣም የለሰለሰ ተቃውሞ እያሰሙ በፓርላማ መሳተፍና በረዥም ሂደት ብዙ መቀመጫ በመያዝ ለውጥ እናመጣለን በማለት የሚደርግ የትግል ስልት ነው። እነዚህ አይነቶች ታጋዮች የሚከፍሉት መስዋዕትነት ከዛቻና ከማስፈራራት የዘለለ አይደለም። በአፍ እላፊ ክርክር ሊታሰሩና ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው ይችል ይሆናል። እንደነዚህ አይነት ለማዳ ተቃዋሚዎችን መንግስትም ለውጭ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካ ለደጋፍ ማሰባሰቢያነት ስለሚጠቀምባቸው እንደ ደህና ጥገት ይቆጥራቸዋል።
2. በመንግስትና በመንግስት አካሄድ ላይ የፖሊስ ልዩነት አለኝ ፤ ይህን ልዩነቴን በሰላማዊ መንገድ ለህዝቤ በማስተማርና በማደራጀት ለተሻለ መንግስትና ዴሞክራሲያዊ ግንባታ የምታገል መሆኔን ማሳየት አለብኝ ብሎ፤ ይህን ልዩነት ይዞ በአገሩ መሬት ላይ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው። ይህ አይነቱ ድርጅት ምርጫ በመጣበት ጊዜ ብቻ የሚንቀሳቀስና እስከዚያው ድረስ በፓርላማ ዉስጥ ጎዝጉዞ የሚተኛ ሰሞናዊ ድርጅት ሳይሆን ከምርጫ በኋላም በቀጣይነት ህዝብን እያደራጅ ለሐቀኛ ዴሞክራሲና ህዝባዊ መንግስት ግንባታ በሐቀኛ ተቃዋሚነት የሚታገል ድርጅት ነው ። ይህን እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ጊዜ ተጨባጭ ሁኔታዎችንና የህዝብን ፍላጎትና ለሚደርገወ ዴሞክራሲያዊ ትግል ምን ያህል ዝግጁነት እንዳደረገ እየገመገመ አስፈላጊ የሆነውን የሰላማዊ እርምጃ እንደሚወስድ ይጠበቃል። ለምሳሌ ወቅታዊ መልክቶችን ያዘሉ በራሪ ወረቀቶችን መሰራጨት፤ ህዝብን በአደራሽ ውስጥና ውጭ እየሰበሰበ አቋሙን መግለጽ፤ በሁሉም ህዝብ ዘንድ መልክቶቹ እንዲዳርሱ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስና ማስረዳት። የህዝብ ደጋፍ ሲበረታና ሁኔታዉ የግድ ሲል የርሐብ አድማ መምታት፤ ስራ ማቆም፤ ሰልፍ መውጣት የመሳሰሉና በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ሊነቀንቁ የሚችሉትን ሁኔታዎችን መፈጸም የግድ ይላል። ተቃዋሚው ድርጅት እነዚህን እርምጃዎች ሲወስድ መንግስትም ደግሞ በበኩሉ ሰላምና መረጋጋትን ለማስከበር በሚል ሊወስድ የሚችለውን ርምጃ መገመት አያዳግትም። የሚወስዳቸው ርምጃዎችም የሰልፍ ፈቃድ መከልከል፤ ያድማ መሪናቸው ያላቸውን የድርጅት መሪዎችን ያስራል፤ ሰልፈኛውን በአድማ በታኝ ወታደር ያስደበድባል፤ ወደ

እስር በት ይወርውራል፤ ከረር ሲልበት ድግሞ ይገድላል። በድርጅት መሪዎች ላይ የተለያየ ወንጀልና የሌለ ስም በመለጠፍ ቅስቀሳ ሊያደርግ ይችላል። ለምሳሌ ከውጭ የድፕሎማሲው ዓለም ጋር ለማጋጨትና ደጋፍ ለማሳጣት አሸባሪ ናቸው የሚል ክስ ይነዛል፤ ህብረተሰቡም ድጋፍ እንዳይሰጥ ለማድረግ ያልተቀጠበ ማስፈራራትና ወከባ ያደርጋል። እንዲህ አይነቱን እርምጃ የዘረኛው የደቡብ አፍሪቃ መንግስት በአፍሪቃ በሔራዊ ኮንግረንስ ላይ በከፍተኛ ደርጃ ፈጽሞበታል። ሰልፍ የወጣውን ህዝብ መደብደብ፤ ማስገደል፤ መሪዎችን ማሰርና ማሰቃየት፤ ድርጅቱን ሰዎች እንዳይጠጉት ለማድረግ ማስጨነቅ፤ የነማንዴላን ድርጅት ኮሚኒስት ናችው በሚል ፕሮፖጋንዳ የምዕራቡ አለም እንዲጠላቸው ከፍተኛ ደጅ ጥናትና ውትወታ አድርጓል።

ስለዚህ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ወደ ሰላማዊ የትግል ሜዳ ሲገባ ይህን ሁሉ ከግንዛቤ ውስጥ አስገብቶና አስፈላጊውን፤ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋትነት ለመክፈል በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ባህሪያት አመዛዝኖና አባላቱናን ደጋፊዎቹን ለዚህ ግብና መስዋዕትነት አዘጋጅቶ መንቀስቀስ ይጠበቅበታል። ይህን ሁሉ ተቀብለው በሰላማዊ መንግድ የአገራቸውን አምባገነን መንግስት በህዝብ ማዕበል ያወረዱና ህዝብን ለስልጣን ያበቁ አገሮችን ስናጤን የሰላማዊ ትግል ከትጥቅ ትግል በሚያንስ መስዋዕትነት ጥሩ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል እንረዳለን።

አሁን ባለው ዓለማችን ያለውን ነባራዊ ሁኔታና የኃይል አሰላለፍ ስንመርምር ሰላማዊ የትግል ስልት ከሌላው አማራጭ ይልቅ ሚዛን የደፋ ሆኖ እናገኘዋለን። አንዳንድ የፖለቲካ ትንታኞች ሰላማዊ የትግል ስልት ሁኔታ ሲያስግድድ ነው እንጅ ትግስት አስጨራሺና የግለሰቦችን ሞራል የሚፈታተን የትግል ስልት ነው ይላሉ፤ ምክንያቱም በአፋኝ መንግስት በኩል የሚደርሰውን ወከባና ገላሰባዊ ስሜትን የሚነካ ውርጅብኙን በማሰብ ነው። ስለዚህ ነው ሰላማዊ ትግል ጠላት ብትር ሲያነሳ አንገትን ደፍተህ የምታልፍበት ቀጭን መሿለኪያ መንገድ ነው የሚሉት።

የሰላማዊ ትግል የሚያስከፍለውን ዋጋ በአጠቃላይ መልኩ ለማየት ሞክረናል፤ ታዲያ ድርጅታችን ኢ ህ አ ፓ (ዴሞክራሲያዊ) አሁን ባለው የአገራችን ሁኔታ አገር ቤት ገብቶ በሰላማዊ ተቃዋሚነት መንቀሳቀስ አለበት የሚል ግፊት ከብዙ አባላቱና ደጋፊዎቹ ይሰማል። እንዲያውም አንዳንድ ደጋፊዎቻችን ከአገር ርቃችሁ ወያኔን በወንጭፍ ድንጋ ልትጥሉ ነው ወይ? የኢትዮጵያ ህዝብ እየረሳችሁ ነው፤ እናንተ ከማንኛውም የተቃዋሚ ድርጅት በበለጠ ጥራት ያለው ፖሊሲ እንዳላችሁ በሁሉም ዘንድ ያታመናል፤ ታዲያ የምትከተሉት የትግል ስልት ውጤት አለማምጣቱን እያያችሁ ውጭ ብቻ በመቀመጥ የህቡዕ ትግል ለውጥ ያመጣል ብላችሁ ከሆነ

አይሰራም፤ ውድቀታችሁን እየጋበዛችሁ ነው ይላል። በርካታ አባላትም በሰላማዊ ትግል ገብተን ታግለን አንድ ውጤት ካላመጣን እንደነ እያሱ ቡድን በርቀት ተቀምጠን እድሚያችን እየቆጠርን ነው ይላሉ። ለዚህ ምሳሌ በአራተኛዉ ጉባዔ የሰላማዊ አማራጭን መያዝ አለብን በሚል የተደረገውን የተጋጋለ ውይይት ማጤን በቂ ይመስለኛል። የትጥቅ ትግል በአሁኑ ዘመን በስም ብቻ እንጅ ውጤትና እድገት እያሳየ አይደለም። ለምሳሌ በላቲን አሜሪካና በደቡብ ምስራቅ ዔሺያ አገሮች የሚያዝግመው የትጥቅ ትግል ከአመት አመት እየደከመ እንጅ አንድ ርምጃ ሲራመድ አይታይም። እንዲያዉም በአሸባሪነት እየተፈረጁ ከዓለም ዴሞክራሲያዉ እንቅስቃሴ እንዲነጠሉ ከፍተኛ ርብርቦሺ እየተደረገባቸው ነው። ወዳጅና ድጋፍ የሚያሳዩዋቸው መንግስታትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም እቀባና ጫና እየተደረገባችው ስለሆነ በሙሉ ልብ ድጋፍ ሊለግሷችው አልቻሉም።

በሌላ በኩል የሚሰማው ደግሞ በአሁኑ ሰዓት ወያኔ እንኳን ከህግ ውጭ ያደረጋቸውን ድርጅቶች ፈቅዶ አስገብቶ ሌላ የራስ ምታት ሊጨምር ይቅርና አገር ቤት የሚንቀሳቀሱትንም ከፍተኛ የሆነ ወከባ እያደረሰ መሆኑ እሙን ነው። ወ/ሪት በርቱካንን በአንካሳ ምክንያት አስሮ እያጉላላና ድርጅቷንም እያዳከመ ነው። ለጊዮኑ የላማዊ ጥሪ ስብሰባ የሄደውን አበራ የማነ አብን ያለምንም ተጨባጭ ክሥ አስሮ እያማቀቀ ነው። ስለዚህ ኢ ህ አ ፓ አሁን አገር ቤት ካሉት ድርጅቶች ሁሉ በላቀና በጠራ ሁኔታ ህዝቡ አድራጅቶ ሊያስነሳበት እንደሚችል ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ወያኔ በጭራሽ ሊፈቅድ እንደ ማይችል የታመነ ነው። እንዴት አድርጎ ነው ኢ ህ አ ፓ (ዴሞክራሲያዊ) የወያኔን ልብ ሰብሮ ህጋዊ ተቃዋሚ ሆኖ ሊገባ ይችላል የሚል አመለካከትም ይንጸባረቃል። አንዳንዶች ደግሞ አገርቤት መግባት ማለት ለነእያሱ ቡድን ማረጋገጫ መስጠት ነው። ዘልዝለው ይስቅሉናል ይላሉ። ለዚህኛው አመለካከት እንደ መፍትሔ የሚሰነዘረው ይህን ይመስላል

1. ኢ ህ አ ፓ (ዴሞክራሲያዊ) የሰላማዊ ትግል የሚለውን የመታገያ ስልት አጥርቶ መያዝና የውጭ መንግስታትንና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞችን በማግባባት በወያኔ ላይ ጫና ማስደረግ ይችላል

2. የተቃዋሚውን ኃይል አስተባብሮ የውጭ መንግስታትን ምክንያት እስኪያጡ ድረስ መግፋት

3. በቀጥታ ወያኔን በህቡዕ በመገናኜት ንግግር ማድረግ

4. በሶስተኛ አካል ማስጠየቅ

5. ሁኔታዎች ከተመቻቹልን የነ እያሱ (ለውጥ አጋቹ) ጉዳይ እዳው ገብስ ነው፤ ምክንያቱም አገርቤት እንዳንገባ የሚወተውቱትን ህዝብን አደራጅተን እነርሱን ከትግል አውድማ ውጭ ልናደርጋቸው እንደምንችል ስለሚረዱ ነው። ያንደ ስሞን ጭሆታቸውን መቋቋም ይቻላል።

አንዳንድ ጓዶቻችን ደግሞ ጭልጥ ብለን ሰላማዊ በሚል ሁለገብን የትግል ስልታችን ለቀን የሰላሙ መንገድ ካልሰራ ያለ ትግል ስልት አማራጭ ልንቀር እንችላለን የሚል ስጋታቸውን ይገልጻሉ። ወንጠፍቴን ላላገኝ ጥንሥሴን ነገርኳት እንዳለችው አርሷ አደር እንዳንሆን የሚል ጭንቀታችውን ይገልጻሉ። አንዲት አርሶ አደሪት የጠላ ጥንሥስ ጠንስሳ የጥንስሷ ማጥለያ ወንጠፍት ታጣለች፤ ስለዚህ ስለጥንስሷ ለጎረቤቷ መንገር ያልፈለገችው አርሶ አደሪት የግድ ከጎረቤቷ ወንጠፍት ለመዋስ ተገደደችና ወደ ጎረቤቷ ሂዳ እባክሺን ወንጠፍት አውሺኝ አለቻት፤ ጎረቤቷ በማዝን ወንጠፍቴን እማ ሌላ ሰው ተውሶ ወስዶታል ብላ በማስተዛዝን መለሰችላት። ስለዚህ ነው ባለጥንስሲቱ ከላይ የተገለጸውን አባባል የተጠቀመችው። ይሁን እንጅ የሰላሙን ትግል ብቻ መያዝ ያለ አማራጭ ያስቀረናል ብለው ለሚጨነቁ ጓዶቻችን የሚስጥው አስትያየት እንዲህ ይላል፤

ኢ ህ አ ፓ ሲመሰረት ሁለት የትግል አማራጭ ይዞ አይደለም የተመሰረትው ስለሆነም፤ ሁለ ገብ የሚል ስልት አልነበርውም። በሰላማዊ መንገድ ትግሌን መቅጠል አልችልም ብሎ ባስበበት ወቅት ሁኔታዎችን አመቻችቶ ኢ ህ አ ሠን መስርቶ የትጥቅ ትግሉ የሚፈልገውን ሁኔታ አሟልቶ ተንቀሳቅሷል። ስለዚህ ወያኔ በሰላም አትንቀሳቀሱም ፤ በህጋዊ መንገድ አገራችሁን አትረግጧትም ካለ ወደ ትጥቅ ትግሉ ለመዞር ኢ ህ አ ፓ (ዴሞክራሲያዊ) የማነንም ፈቃድ አይጠቅም። የሚያጣው ነገር ቢኖር የጠየቀውን ጥያቄ ብቻ ነው። ስለዚህ የአባላትን ጉባዔ ሳይጠብቅ አመራሩ ሁኔታው ከተሟላ ለአባላት እያሳወቀና ሐሳባቸውን እያስተናገደ የድርጅቱን መርሆ ወደ ትጥቅ ትግሉ ሊያስትካክል እንዲችል አሁን የሚደረገው የአባላቱ ጉባዔ ስልጣን ሊሰጠው ይገባል የሚል እምነት ይንጸባረቃል። እንዲያው በአሁኑ ወቅት ሁኔታው የማይፍቅደውን የትግል ስልት ሙጭጭ ብሎ ይዞ መቀመጥ "ሎሚ ካልመጠመጡት እንቧይ ነው" እንደሚባለው ይሆናል። መዘንጋት የሌለብን ወያኔ እኮ የትጥቅ ትግል የምትለዋን ዘርፍ ይዞ አሸባሪ ናቸው ብሎ ሊያስፈርጀን እንደ ሚሞክር ማዎቅ አለብን። ይህን ደግሞ ብዙ ጊዜ ሞክሯል።

ኢ ህ አ ፓ (ዴሞክራሲያዊ) በሰላማዊ አማራጭ ብቻ ቢታግል የሚያገኘው ጥቅምና የሚያጋጥሙት ችግር ምን እንደ ሚመስሉ እንመልከት

## ጥቅሙ

1. ኢ ህ አ ፓ ምንም ወዳጅ ዘመድ አለው ብለን ባንተማመንም በዓለም መንግስታትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ዘንድ ከዚህ በፊት ሲከተለው ከነበረዉ ሁለገብ የትግል አማራጭ ወጥቶ ለሰላም ብቻ ዝግጁ መሆኑን በማስረዳት ከወያኔ በኩል በትጥቅ ትግል የሚያምን ነው በማለት የሚያደርገውን ቅስቀሳ ዋጋ ያሳጣዋል። እነዚህ መንግስታትም ለምን ኢ ህ አ ፓን አትፈቅዱለትም በማለት ደፍረው እንዲጠይቁት ይረዳል

2. አገርቤት የመግባቱ እድሉን ካገኜን ለወጣቱ ትውልድ የድርጅታችን ማንነቱን በይፋ እንዲያስተምርና ታሪካዊ ዓላማዉን ሊያስርክብ እንዲችል ይረዳዋል

3. ልጆቻቸው በኢ ህ አ ፓ ተሰልፈው መስዋዕትነት የከፈሉ ቤተሰቦች ኢህ አፓን እንደ ትልቅ ሀውልት በልባቸው ሰንቀው የኖሩትን ሁሉ ድጋፍ ሊያገኝ ይችላል።

4. አገር ቤት የሚኖሩ የቀድሞ አባላቱ እንዲ ደግፉትና በሂደት እንዲቀላቀሉት እድል ይሰጣቸዋል

5. በሰላማዊ ትግል ቀሰበቀስ ችግሮችን በውይይት፤ በክርክር በመፍታት አቋሙንም በቀላሉ ሰፋ ላለ ህዝብና ክልል ለማዳረስና ለመቀስቀስ ያመቸዋል

6. በሰላሙ መንገድ መቀጠል ቢያቅተውም እንኳን የህቡዕ መዋቅሩን እንዲያጠናክር እድል ያግኛል

7. በውጭና በኀረቤት አገር ያሉ አባላቱን ሞራል ሊያስጠብቅና እስከመጨረሻዉ አብረዉት እንዲቀጥሉ ሊያደርግ ይችላል። አሁን ባለበት ሁኔታ ግን የአባላቱና የደጋፊዎች የትግል ስሜት እየተነካ በጥቂት አመታት ውስጥ ከትግል ውጭ የሚሆኑት ቁጥር በቀላል የሚገመት አይሆንም

ለውይይት የቀረበ

8. በትጥቅ ትግል ቢኬድ በጦርነት ሊወድም የሚችለውን የሰው ህይዎትና የአገሪቱ ንብረት ከጥፋት እንዲድን ያደርጋል። የትጥቅ ትግል ወይም ጦርነት አስከፊ ነው። አማራጭ ሲጠፋ ብቻ የሚውሰድ የመጨረሻ እርንምጃ እንጅ ጦርነት አውዳሚ ነው።

9. ወያኔን አንቅሮ የተፋዉና አልኝታ ድርጅት ያጣዉ ህብረተሰብ ቁጥር በጣም ከፍተኛ ስለሆነ ይህን ህብረተሰብ በቀላሉ ወደራስችን ለማድረግ እንችላልን

## ሊደርሱበት የሚችሉ ችግሮች

1. ለረዥም ጊዜ በህገወጥነት ተፍርጆ በመቆየቱ ምክንያት በአገር ቤት ውስጥ ይፋዊ ድጋፍ የሚሰጠው የሰው ሃይል የለም ስለዚህ በሰላም ሲገባ ለተወሰነ ጊዜ ተባባሪ የሚሆነው የሰው ኃይል ችግር ያጋጥመዋል። ጽ/ቤት እንኳ ፈልጎ ለመከራየት የሚረዳ ሰው አይኖርም ምክንያቱም ይህን ያህል ጊዜ ተፈርጆ ከኖረ ድርጅት ጋር አብሮ መታየት ለህልውና ስለሚያስጋ። በሆኑም እንደ ህጋዊ ድርጅት ተመዝግቦ ለመንቀሳቀስ የሚያስፈልገውን በአራት ክልሎች ውስጥ የ500 ሰው ፊርማ ለማቅረብ ይቸገራል። ተምዝግቦ መንቀሳቀስ ካልቻለ ደግሞ ስራው ውሱን ይሆናል።

2. ወያኔ የተለያዩ ችግሮችን እየፈጠረ ክስ በመምስረትና ሌሎችንም እንዲከሱ በማደፋፈር ተዎካዮቻችን እስርቤት ሊያስገባ ይችላ። ይህን ቀውስ ለመከላከል ድርጅታችን ጠበቃ አቁሞ ላይና ታች በማለት እንተጓጎላለን። ይህም ሆኖ ጉዳያችን የሚከታትል ጠበቃም ለማገኘት ልንቸገር እንችላለን ምክንያቱም የወያኔ አፋኞች ግለሰብ ጠበቃዎችን በማንገራገር ድርጅታችን እንዳይ ወክሉ ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህን ደግሞ በቅንጅት ላይ ያደርጉት እንደነበር ጉዳዮን በቅርብ የተከታትሉ አባላቱ ይፋ አድርገዋል። በቆራጥነት ኢ ህ አ ፓ (ዴሞክራሲያዊን) የሚወክል ጠበቃ አንድ እግሩን ከውጭ አገር መሬት ላይ አንዱን እግሩን ኢትዮጵያ ላይ ያደረገ መሆን አለበት። ይህ ችግር ምናልባት በመጅመሪያው ላይ ሊያጋጥመን ሊሆን ይችላል ብለን ተሰፋ እናድርግ ሆኖም ቀላል ግምት የምንሰጠው አይሆንም።

3. ከክፍል ሐገር ወደ ከፍል ሐገር ወይም ከክልል ወደ ክልል ተንቅሳቅሶ ለመስራት የወያኔ ካድሬዎች በልዩ ልዩ ምክንያት ሊያደርሱ የሚችሉት ማንገላታት በቀላሉ የሚገመት አይሆንም። ለአንድ ቀን አግቶ ማዋል፤ ለሳምንት ማሰር፤ መደብደብ፤ ደጋፊዎቻችን ማሰርና መግረፍ፤ ሌላ ደጋፊ እንዳናገኝ እርዳታ ሚያደርጉልንን ሰዎች መቀጣጫ ማድረግ እስካሁን የታዩት የውያኔ ተቃዋሚዉን የሚያዳክምበት ዘዴ ነው። በተለይ ደግሞ በኢ ሀ አ ፓ ላይ የበረታ እንደ ሚሆን ይጠበቃል

4. በወያኔ ተድቦልቡለው የተፈጠሩ የከልል መንግስታትና የጎሳ ድርጅቶችም በእንቅስቃሲያችን ላይ ከፍተኛ ደንቀራ ሊሆኑብን እንደ ሚችሉም ማሰብ ያስፈልጋል።

5. በውጭ የሚቀሩ ድርጅቶች የሚያደርሱት ጫና፤ እንደነ እያሱና እንደነ ግንቦት 7 አይነቶች በውጭው ዓለም በሚኖረው ደጋፊአይችንና አባሎቻችን ላይ ከአሁኑ በበለጠ ቅንብር እስኮር ለመምታት ከፍተኛ ርብርቦሽ በማድረግ አንደኛ የሞራል ተጽዕኖ ያሳድራሉ ሁለተኛ በውጭ ገንዝብ እንዳናሰባስብ በህብረተሰቡ ዝንድ ሊዘምቱብን ይችላሉ

6. ወያኔ ያዘጋጃቸውን መገልገያ ተቋሞቹን በመጠቀም እንቅስቃሲያችን ለገድብ ይችላል። ለምሳሌ በሰራተኛው አካባቢ ባደራጃቸው ሰዎቹ፤ በወጣቱ፡ በገበሬ ማህበሩ አማካይነት ሊፈጽምበን የሚችለው ጊድራ ቀላል አይሆንም። አንድ ምሳሌ ላንሳ፤ የገበሬ ማህበር ሊቀመንበር፤ ምክትል ሊቀመንበር፤ ጸሐፊው የወር ደመዎች ከመንግስት ይቆረጥላቸዋል። ይህ ብቻ አይደለም መሬታቸውን የአካባቢው ገበሬ በነጻ አርሶ ያመርትላቸዋል። ስለዚህ ወያኔ የራሱ የሆነ የመሬት ከበርቴ እየፈጠረ ነው። ይህን የሚያደርገው ለገበሬው አዝኖ ሳይሆን ለራሱ አይንና ጆሮ በከበሬው ህብረተስብ እየፈጠር ነው።

7. የገንዝብ ችግር ከፍተኛዉና አሳሳቢው ደንቀራ ሊሆን እንደሚችል ካለው የድርጅታችን የገንዝብ ሁኔታ የሚያስገነዝበን ይሆናል። ገንዝብ ለምን ለምን ያስፈልገናል
    - ጽ/ቤት ለመከራየት
    - ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ ለማደራጀት
    - አደራጆችንና በጽ/ቤቶች የሚሰሩ ሰራተኞችን ለመደጎም
    - በራሪና ድርጅታዊ ወረቀቶችን ለማባዛትና ለማስራጨት

- ለመጓጓዣና
- ለሆቴል
- ለጽህፈት መሳሪያዎች ወዘተ

እስካሁን ድረስ በተቃዋሚነት ከተንቀሳቀሱ ድርጅቶች ውስጥ ከደጋፊዎቹና ከአባላቱ ከፍተኛ ገንዝብ ስብስቧል ተብሎ የሚጠረጠረው ቅንጅት ይመስለኛል ይሁን እንጅ በጽ/ቤቱ ውስጥ ከቀን ቀን የሚሰሩትን የጽፈት ቤታችውን ሰራዎች ከሰሩት ሰው " ቅንጅት ከየት ወደ የት" በሚል እርዕስ ከጻፋት መጽሐፍ ላይ እንደ ዘገቡት ቅንጅት ከነበረው ከፍተኛ ችግሮቹ አንዱና ትልቁ ችግር የገንዝብ ችግር እንደ ነበር ይገልጻሉ። ለምሳሌ በአንድ ወቀት ብቻ 1,284,692.10 በላይ የኢትዮጵያ ብር በቅንጅት አካውንት ውስጥ እንደገባ ይገልጻሉ፤ ሆኖም በአገሪቱ ደረጃ በቋሚነት የሚንቀሳቀሱ አባላቱን ለተወሰነ ጊዜ እንኳ ለመደጎም ችግር እንደነበር ገልጸዋል። አያይዘውም አብዛኛው ስራ የሚሰራው በፈቃደኞች እንደነበርም ይጠቅሳሉ። ስለዚህ ገንዝብ ከሌለ ስራ ሊሰራ እንደ ማይችል ከወዲሁ መታሰብ አለበት ለማለት ነው።

ወያኔ የምንፈልገዉ ሁሉ አድርጎ እንድንጋባ ቢፈቅድ ኢ ህ አ ፓ (ዴሞክራሲያዊ) በ 2002 ምርጫ ሊሳተፍ ይችላል ወይ? ለዚህ ጥያቄ ይቻላል ውይም አይችልም ብሎ አጭር መልስ መስጠት ይቻላል ነገር ጎን ምርጫ ለመሳተፍ ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን መመርመር ያስፈልጋል። ለምሳሌ ከላይ ለመጥቀስ እንደ ተሞከረው የውድድር ሜዳው መስናዳቱን፤ ማለትም የምርጫ ኮሚሽኑን አወካከል፤ የሚዲያ አጠቃቀምን የመሳሰሉ ጉዳዮች እንኳ ወደ ኋላ አስቀርተን ሌሎችን ቀለል ያሉ፤ ድርጅታችን ሊያሟላ የሚገባውን ብቻ ብንመለከት በቂ ግንዛቤ ሊሰጠን ይችላል። ምርጫ ሲገባ እንዲሁ ለይስሙላ ምርጫ ገባ ለመባል ሳይሆን ህዝብን ዳር እስከዳር አንቀሳቅሶና አደራጅቶ ለማቸነፍ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህ 2002 ምርጫ ማለት ከአንድ ዓመት ያነሰ ጊዜ ነው፤ ስለዚህ በዚች አጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉን ነገር አዘጋጅቶ መርጫ መግባት አይቻልም የሚል የግል አስተያየት አለኝ። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የሰው ኃይል፤ የገንዝብ ኃይል፤ እና የመሳሰሉ ችግሮችን አሟልቶ ለምርጫ አይደረስም። ስለዚህ መታየትና መታለም ያለበት ከምርጫ ባሻገር ለሚገኝ ሕዝባዊ ዝግጅት ነው።

በዝች ጽሁፍ ውስጥ ለሚኖሩ ግድፈቶች ተጠያቂነቱ የኔ ብቻ መሆኑን እንድት ገነዘቡልኝ አደራ እላለሁ

ለወጥ የቀበል

**አቡኔ**

ለውይይት የቀረበ